# ኤርትራ - ያልተሞከረ መንገድ

ዳደ ደስታ

03-16-16

ከጦርነቱ በኋላ የኤርትራ ጉዳይ ከኢትዮጵያ ስትራተጂካዊ ጥቅሞችና ስጋቶች አኳያ ተገቢ ዕይታ፣ ክትትልና ማስተካከያ እያገኘ መጥቷል የሚል እምነት የለኝም። የኤርትራ ዜጎች ወደ አውሮፓ የሚፈልሱትን ያህል ኤርትራ ራሷ በጂኦፖለቲካ ደረጃ ወደ ዓረቡ ቀጠና እየተንፏቀቀች እናያለን። ይህ ለኢትዮጵያ አሳሳቢ መሆን አለበት። በዚህ ምክንያት ሊሆን ይችል ከነበረውና ካመለጡት ዕድሎች አንጻር ሲታይ የእስከአሁኑ ኪሳራ አላነሰም፣ ይህ እንግዲህ ሁኔታዎች በዚህ ከቀጠሉ ደግሞ ኪሳራው እየሰፋ ይሄዳል ከሚል መንደርደርያ የሚነሳ ፖሊሲ ጠቋሚ ማስታወሻ ነው። ማስታውሻው ትንታኔዎች፣ መደምደምያዎችና መፍትሄዎች የጠቆመ ዝክረ ሃሳብ ነው።ለኢትዮጵያው ጠ/ሚ/ር በተለይ በማሳሰብያ መልክ የቀረቡ አዳዲስ ነጥቦችም ተካተውበታል።ማስታወሻው የተባሉትን ቁምነገሮች ለማስረገጥ ሲባል የኤርትራ መንግስት የፖሊሲ ውሳኔና ምርጫ፣ ፖሊሲዎቹን ለማሳካት የሚሄደው ርቀት ምን ድረስ እንደሆነ፣ የኢትዮጵያና የኤርትራ ግጭት አነሳስና ጦርነት- ከተከተለው የጦርነቱ ውጤትና የሰላም መፍትሄ የማይገናኝ ስለመሆኑ፣ የድንበር መካለሉና ሌሎች ጉዳዮች አሁን ካለው የኤርትራ መንግስት ጋር በትብብር ለመፍታት የቀረችው ብቸኛ መንገድ፣ ስለሌሎች የፖሊሲ አማራጮች፣ ጉርብትናን ለማጠናከርና ለማደስ የሚሰራ ተቋም የማቋቋም ስትራተጂክ አስፈለጊነት አካቶ ይዟል። የኤርትራ ጉዳይ ብዙ ሃብት፣ ጊዜ፣ ዕድልና ትውልዶች የበላ ሁኖ ሳለ ዛሬም ድረስ ችግር ሆኖ አብሮን አለ። ለኢትዮጵያውያን ከዚህ በላይ የሚታይ አንገብጋቢ አገራዊ ጉዳይ ብዙ አይደለም። በፖሊሲ ማመንጨትና ማስፈጸም ላይ ያላቹህ ሙያተኞችና ባለስልጥናት ሁሉንም አንብባቹህ የቀረቡት የፖሊሲና የመፍትሄ ሃሳቦችን በጥሞና እንድታጤኑዋቸው እጋብዛለሁ። ሁሉንም ለማንበብ የጊዜ እጥረት ያለባቹህ አንባቢዎች ግን አዳዲስ ሃሳቦች ያሉባቸውን ወደ ማጠቃለያው ያሉት ገጾች ብቻ ብታነቡ በቂ ሊሆን ይችላል። ሁኔታዎች ሲለወጡ ፖሊሲም መለወጥ ተገቢ ነው የኢትዮጵያ ጠ/ሚ ኃይለማርያም ባለፈው ሳምንት ለፓርላማቸው ሲናገሩ በኤርትራ ላይ የመንግስታቸው ፖሊሲ እንዳልተለወጠና ከ **11** ዓመታት በፊት የወጣውን ባለ አምስት ነጥብ የሰላምና የድርድር ጥሪ በቦታው እንዳለ ገልጸዋል። ኢትዮጵያ ላለፉት አሰርት ዓመታት በኤርትራ ላይ የፖሊሲ ለውጥ ሳታደርግ መቆየቷ እንደድክመት እንጂ እንደጥንካሬ የሚታይ አይሆንም። ምክንያቱም ኤርትራ ውስጥና ከኤርትራ ጋር የተገናኙ ሁኔታዎች ባለፉት **10** ዓመታት የፖሊሲ ለውጥን የሚጋብዙ በርካታ ክስተቶችና ጂኦፖለቲካዊ መስተጋብሮች ተስተውለዋል። የእውነታዎች ለውጥ ሲኖር የአቋሞች ለውጥና ሽግሽግ ማየት የግድ ይላል። ባለ አምስት ነጥቡ የሰላም ሃሳብ የድንበር ኮሚሽኑ ሳይፈርስ፣ አንሚ የተሰኘው የጥበቃና የማካለል ሂደት እንዲያመቻች ሃላፊነት የተሰጠው አካል ሳይባረር፣ አንሚ ከኢትዮጵያ መከላከያ በአደራ የተረከበው ጊዚያዊ የጸጥታ ቀጣና ሳይጣስ፣ የካሳ ኮሚሽኑ የኤርትራን ወራሪነት አረጋግጦ ሳያውጅ ነበር። የአልጀርሱ የሰላም ስምምነት ማእከላዊ ቁምነገር ሰላም ማውረድና ጸብ ማቋረጥ እንደነበር ልብ ይሏል። ጸብ ግን ተቋርጦ አያውቅም፣ ሰላምም ሁሌ እንደታወከ ነው ብቻ ሳይሆን በኤርትራ የጦርነት ዓቅም መሟጠጥና በአልጀርሱ የሰላም ስምምነት ምክንያት የተገኘው ዕድል ባክኖ ቀርቷል። ሁለቱ አገሮችም ከጦርነቱ ማብቃት በኋላም ወደ ሙሉ ሰላምና መልካም ጉርብትና መመለስ ሳይችሉ መቅረታቸው የሚቆጭ ብክነት ነው። ባለ አምስቱ ነጥብ የሰላምና የድርድር ሃሳብ ለአልጀርሱ አጠቃላይ የሰላም ስምምነት እውቅና በመስጠት የሄይጉ ኮሚሽን በሰጠው የድንበር ማካለያ ብይን አተገባበር ላይ በምክክር ስለማካለልና የኢትዮጵያና ኤርትራ ግንኙነት ወደ መደበኛ የጉርብትና ሁኔታ

ስለመመለስ የሚያብራሩ ነጥቦች ያካተተ ነበር። ይህ የሰላም ሃሳብ የኢትዮጵያ መንግስት ለሁለቱ አገራትና ለአከባቢው ዘላቂ ሰላምና ልማት ይበጃል ብሎ አውጥቶ አውርዶ እስከወጠነዉ ድረስ ሰፊ የፖለቲካ ስራ ሰርቶ የኢትዮጵያና የኤርትራ ህዝቦች የመታገያ ሀሳብ እንዲያደርጉት፣ በተጠናከረ የዲፕሎማሲ ጥረት የአህጉሩና የዓለም ኀይሎች ዋጋ እንዲሰጡት ማድረግ ነበረበት፡፡ አንዴ ገበያ ወጥቶ አልሸጥ ያለን ዕቃ በማያቋርጥ ጥረትና ብልሀት ከእጅ ለማውጣት መትጋት እንጂ የትም ጥሎ ቆይቶ "ገዢ ከተገኘ"ኮ ያ ነገር አሁንም አለ" ማለት የምር እንዲያምር ሳይሆን እንዳይቀር ያህል ይመስላል፡፡ እነዚህን ነጥቦች የያዘው የኢትዮጵያ የሰላም ጥሪ የኤርትራ መንግስት ስላልተቀበለውና ኢትዮጵያን በተዘዋዋሪና በቀጥታ ማወክ እንደስትራተጂ ይዞ መንቀሳቀስ ስለቀጠለ፣ ኢትዮጵያ መጀመርያ በአህጉራዊና ዓለማቀፋዊ መድረኮች እንዲወገዝ፣ እንዲገለልና እንዲቀጣ ባደረገችው ትግል የኤርትራ መንግስት ላይ እስከ ማዕቀብ የደረሰ ጫና መፍጠር ችላ ነበር። ይህም ቢሆን የኤርትራ መንግስት ላይ ያመጣው የባህርይም ሆነ የስትራተጂ ለውጥ ሲታይ እምብዛም ነው። በዚህ ምክንያት የኢትዮጵያ መንግስት "ተመጣጣኝ ቅጣት" በሚል ሁለት ተጨማሪ የምላሽ ማጠናከርያ አቋሞች በቆየው ፖሊሲ ላይ ጨምራ የኤርትራን የህውከት ፖሊሲ ለመከላከል ሞከረች። እነዚህም ሁለት አቋሞች አንዱ የኤርትራን ተቀዋሚዎች በአደራጃጀት ደረጃ አጠናክሮ የኤርትራን የለውጥ ትግል እንዲመሩ ማስቻል ሲሆን ሁለተኛው ለእያንዳንዷ የኤርትራ ግልጽ ትንኮሳ በምላሹ ተመጣጣኝ የኃይል እርምጃ መውሰድ የሚሉና ሁሉም እስከአሁን እየተሰራባቸው የቆዩ ፖሊሲዎች ናቸው።የኤርትራ መንግስት አመቺ ሁኔታዎችን እየጠበቀ አከባቢዉን የማተራመስ ተግባሩን ከማስቆም አንፃር ግን ውጤታቸው ያን ያህል አመርቂ አለመሆኑ እስካሁን ከታዩት ትንኮሳዎች ማየት ይቻላል። ባለ **5** ነጥቡ የሰላም ጥሪ ላለፉት **11** ዓመታት ያልተቀበለው የኤርትራ መንግስት ከአሁን በኋላ ይቀበለዋል የሚያሰኝ አንዳች ምልክት ወይም ምክንያት አይታይም። የመገለሉና የማዕቀቡም ቅጣት ቢሆን የኤርትራ መንግስት ለውግዘት የዳረጉትን አፍራሽ አደፍራሽ ተግባራቱን ከግልጽ ወደ ህቡእ ከቀን ወደ ጨላማ እንዲያሸጋግር አስገድደውት ቢሆን እንጂ ወደ ጤናማ አቅጣጫ ሊመሩት እንደማይችሉ አሁን ከበቂ በላይ ግልጽ ሆኗል። የኤርትራ ተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅቶችም ከራሳቸው ውስጠ-ድክመት፣ ከኢትዮጵያ መንግስት ድጋፍ ማነስና ከኤርትራ መንግስት ደህንነት መሰሪነት አንጻር ለዓመታት ተንቀሳቅሰው ያስመዘገቡት ውጤት ከዜሮ እስከ ኢምንት ነው። ከኃይል እርምጃ አንጻር የሚሰጠው ተመጣጣኝ ምላሽም "ተመተን ዝም አላልንም" ከማለት ያለፈ ፋይዳ አልነበረውም። ለምሳሌ የኤርትራ መንግስት ከ **4** ዓመታት በፊት የታጠቁ ኃይሎችን አሰልጥኖ በመላክ ዓፋር-ኢትዮጵያ ውስጥ የነበሩትን ጎቢኚዎች አሳፍኖ ወሰደ፣ጥቂቶችንም አስገደለ። ኢትዮጵያ በእርግጥ ያኔ "ተመጣጣኝ"ያለችውን እርምጃ ወሰዳ ነበር። ነገር ግን የኤርትራ መንግስት አድፍጦ ቆይቶ አሁን በቅርቡ በኦሮሚያ አካባቢ የተነሳውን ዓመጽ ከመነሳት ጋር በተፈጠረው ሁኔታ የኢትዮጵያን መንግስት ድክመት ለመፈተሽ ወስኖ ከ **40-85** ዜጎችን አፍኖ እስከመውሰድ ደረሰ። ያሰበውን ዓይነት ድክመት አለመኖሩ ሲገነዘብ ደግሞ ዜጎቻችንን አንከራቶ በሱዳን በኩል እንዲመለሱ አደረገ። እዚህ ላይ ያለው ትክክለኛው መልእክት የኢትዮጵያ መንግስት የተዳከመና የተወጠረ የመሰለው ወቅት የኤርትራ መንግስት ደፋር ትንኮሳ ከማድረግ ወደ ኃላ እንደማይል ነው። ሌላው የኢትዮጵያን ድክመት አጋንኖ ለማሳየትና በኢትዮጵያውያን መካከል ጥላቻና መጠራጠር ለመፍጠር ብዙ ሃብት መድቦና የሚድያ ተቋማት አደራጅቶ በስፋት የሚሰራበት ከዋነኛ መንግስታዊ ተግባራቱ አንዱ የሆነ ይመስላል። የኢሳት ሳተላይት ቴሌቪዥን ፕሮግራሞች ይዘትና ኢዲቶሪያላዊ አቅጣጫ የሚመራው ግንቦት **7** ቢሆንም ሙሉ በጀቱን የሚያገኘው ግን ከኤርትራ መንግስት ነው። እርግጥ የኤርትራ መንግስት ይህንን ገንዘብ ያገኘው ከግብጽ እንደሆነ ከዶ/ር ብርሃኑ ነጋ አንደበት ሾልኮ ከወጣው መረጃ ተገንዝበናል። በሜኖሰታ ግዛት ለሚገኘው የኦሮሞ ሚድያ ኔትዎርክ ከኤርትራ የተመደበለት በጀት ብቻ ሳይሆን የተሰጠው ተልእኮም አስገራሚ ነው። የኤርትራ መንግስት የኦህዲድን ኢህአዴግነት በሶሻል ሚድያ ማላላት፣ ብሎም ከኢህአዴግ መነጠል ይቻላል በሚል ስሌት ያን ያህል ገንዘብ ለአንድ ብዙም ለማይታወቅ የሶሻል ሚድያ ኔትወርክ መድቦ መንቀሳቀሱ የህልም ጉዞ

ሊመስል ይችላል። ነገር ግን ይህ የኤርትራ መንግስትን ቀዳሚ ትኩረት ምን እንደሆነ የማያከራክር ማሳያ ነው። ከግብጽ እስከ ኳታር፣ ከአልሸባብ እስከ ግንቦት ሰባት፣ ከኦነግ እስከ ኦብነግ፣ ከኢሳት እስከ **OMN** ያሉትን አካላት እያቀያየረ ወይም እያቀናጀ ይጠቀምባቸዋል። ቁምነገሩ የኤርትራ መንግስት ዋናው ትኩረቱ ከኤርትራ ይልቅ ኢትዮጵያ፣ ከአዎንታ ይልቅ አፍራሽ ሆኖ መዝለቁና እንደዛ ሆኖ እንደሚቀጥል መገንዘቡ ላይ ነው። ለዚህ ተልእኮው የሚጠቀምባቸው ስልቶችና ሁኔታዎች የተለያዩ መሆናቸው ያፖሊሲውና የዓላማው መለያየት አይጠቁምም። ይህ ማለት ተመጣጣኝ ምላሽ የተባለውፖሊሲ ትንኮሳንና አፍራሽ ተግባራትን እንደ ዋነኛ ስራው በያዘ አንድ መንግስት ላይ ውጤታማ ሊሆን ይችላል ብሎ ማለት የኢትዮጵያም መንግስት የኤርትራን እያንዳንዷ የመተንኮስና የማተራመስ ተግባርን በተግባር ለመመለስ ዋነኛና ቅድሚያ የሚሰጠው ተግባር ሆኖ የመንግስት የቅድሚያ ትኩረት እያገኘ ይቀጥላል የማለት አንድምታ አለው። ይህ ግን ኢትዮጵያን ከድህነትና ከኃላቀርነት ወደተሻለ ተስፋና ኑሮ ለማሸጋገር ለሚተጋ መንግስት አዋጭ አቅጣጫ አይሆንም። የኢትዮጵያ መንግስት ኤርትራን ወደ ሙሉ ሰላማዊነትና መልካም ጉርብትና መመለስ ከኤርትራ መንግስት ጋር እኩል የሚካፈለው ግማሽ ኃላፊነት ብቻ እንደተሸከመ ማሰብ የለበትም። እንደዛ ማሰብ ይቻል የነበረው ሁለቱም መንግስታት የሁለቱም ሃገራት ህዝቦች በመልካም ጉርብትናና ሙሉ ሰላም ማጣት ለሚባክንባቸው ዕድል እኩል ተቆርቋሪነት ቢኖራቸው ነበር። የሰላምና የመደጋገፍ ዕድል እንዳይኖር ከሚያንገራግር ኃይል ጋር እኩል ኃላፊነት መሸከም ብሎ ነገር የለም። ስለዚህም የኢትዮጵያ መንግስት እነዚህ ከድህነትና ከኃላ ቀርነት ለመውጣት መትጋት ያለባቸው ሁለት ህዝቦች በመካከላቸው ሙሉ ሰላም የሰፈነበት በመደጋገፍ የሚገለጽ መልካም ጉርብትና መፍጠር ሙሉ ኃላፊነት ለብቻው እንደተሸከመ ማወቅ አለበት። በእርግጥ ውሎ አድሮ የኢትዮፕያም የኤርትራም ህዝቦች ለሙሉ ሰላምና መልካም ጉርብትና የሚደረገውን ማንኛውም ትግል ደጋፊና ባለቤት መሆናቸው የሚጠበቅ ነው። የዓለም ማህበረሰብም ለህዝቦች መልካም ግንኙነትና መደጋገፍ የሚደረግን ጥረት ያበረታታል። እዚህ ላይ ያለው ቁምነገር የኢትዮጵያ መንግስት የኤርትራንና የኢትዮጵያን ህዝቦች ወደ ሙሉ ሰላምና መልካም ጉርብትና የመመለስ ስራና ኃላፊነት በግማሽ መንገድ ድርሻነት ማሰብ የለበትም። የሰይጣን እጅ ኪራይ የህዝባዊ ግንባር አመራሮች ስር ነቀል፣ አንዳንዴም አስደንጋጭ የሆኑ አቋሞች በመያዝና አስገራሚ እርምጃዎች በመውሰድ ከድሮ ጀምሮ የሚታወቁበት አሻራ ነው። ለምሳሌ የፋሽስት ኢጣልያ መለያ ቅርስ የሆኑትን ህንጻዎችና ሃውልቶች በቅርስነት ሲንከባከቡና በዓለም ቅርስነት እንዲመዘገብላቸው ሲጥሩ ይታያሉ። ቅኝ ገዢና ወራሪ የኢጣልያን ኃይል በጀግንነት በመደምሰስ የሚደነቁት የአፍሪካ ጀነራል አሉላ አባነጋን ለማስታወስ ዶግዓሊ ላይ የተሰራው ሃውልት ለማፍረስ የወሰደባቸው ቅጽበት ደግሞ ከብርሃን ይፈጥናል። በዚህ እንቆቅልሽ የተገረመ አንድ ኤርትራዊ ጸሃፊ “የህዝባዊ ግንባር መሪዎች የአንድን ጸረ አውሮጳ ቅኝ ገዢ ኃይሎች በመዋጋት የሚታወቀውን የአሉላን የሚታይ ሃውልት አፍርሰው ለቅኝ ገዢዎቹ ጣልያኖች የማይታይ ሃውልት ተከሉ” ሲል ነበር የገለጸው። ይህ ግን አጠቃላይ የህዝባዊ ግንባር ፍላጎትና ራዕይ በእንደዚህ ዓይነት አጉል እርምጃዎች የተሞላ ነበር ለማለት አይደለም። የህዝባዊ ግንባር መሪዎች ለኤርትራ ህዝብና ለኤርትራ ህዝብ ጥሩ ራእይና ህልምም እንደነበራቸው መካድ ልክ አይሆንም። ውድቀታቸው የሚጀምረው ራእያቸውን ለማሳካት በኤርትራ ዓቅም ልክ ያለማሰባቸውና የሌሎችን ትብብር ለማግኘት ከመግባባት ይልቅ ማስፈራራት እንደትክክለኛ አሰራር ሊጠቀሙበት ከመሞከራቸው ጋር ነው። የኤርትራ መንግስት ባህርያዊ ስሌትና ትኩረት ከመጀመርያው መጥፎ አልነበረም። አፍራሽ ዝንባሌው ኃላ ላይ ከውድቀት ጋር ተቀላቅሎ፣ በሂደትም የበለጠ ትኩረት እያገኘ መጥቶ አሁን አሁን ለኤርትራ መንግስት የሚታየው ብቸኛው የማንሰራራት ሁኔታ ኢትዮጵያ ውስጥ ከሚኖር መዳከምና ውዥንብር ጋር አያይዞ የሚያየው ይመስላል። ይህ የሆነው ከጊዜ በኋላ ነው። የኤርትራ ነጻነት ህዝባዊ ግንባር መሪዎች በነጻነት ገድል ዘመናቸው ያለሙዋት ኤርትራ እጅግ የዘመነች አገር ነበረች። እነሱም ወዳለምዋት ኤርትራ ለመጓዝ በጎ ራእይና ወዳዛ ያደርሳል ያሉትንም መንገድ ቀይሰው ነበር። ስለዕድገት ዕቅዶቻቸው በሚያወሩበት ጊዜ በተደጋጋሚ በምሳሌነት የሚጠቅስዋቸው

አገሮች ስዊድንና ሲንጋፖር እንደነበሩ እናስታውሳለን። ያም ማለት መንግስታዊ ካፒታሊዝም ለመገንባት የነበራቸውን ምርጫና ዕይታ ያመላክታል። የኤርትራ መሪዎች የጨመሩት ነገር ቢኖር የመረጡትን ጉዞና ራእይ ለማደናቀፍ የሚሞክር፣ ወይም የማይተባበር ኃይል ከውስጥና ውጭ እንዳይኖር የሚያደርግ መጠነ-ሰፊ የሚሊቴራይዜሽን ፕሮግራም ማካሄድ ነበር። መሪዎቹ ገና ከጥዋቱ የካፒታሊዝም ግንባታው ገዢ ተዋናይ ደግሞ ፓርቲውና መንግስት እንዲሆኑ ቀመሩ። መንግስቱና ፓርቲው በፋይናንስና ንግዱ ላይ የቀየሱት የሞኖፖል ሚና የኤርትራ መንግስትነት ግንባታ ከተለመደው መንገድ ያፈነገጠ አካሄድ ሆኖ ታየ። ለምሳሌ የዚህ ያልተለመደ አካሄድ ማሳያ አንዱ የኤርትራ መንግስት በ **25** ዓመት መንግስታዊ ዕድሜው አንድም ጊዜ ባጀቱን አሳውቆና አውጆ የማያውቅ መሆኑን ነው። የኤርትራ መንግስት ያልተለመዱ ኢኮኖሚያዊና ፊስካላዊ ፖሊሲዎች፣ አገሪቷ በቀጣናው የምትከተለው ሚሊቴሪስቲክ አካሄድ ነበር ኢትዮጵያንና ኤርትራን ወደ ፍጥጫ፣ ቆይቶም ወደ ውግያ እንዲገቡ ያስገደዳቸው። የኤርትራ መንግስት ኤርትራዊነትንና የኤርትራ ፖለቲካዊ-ማህበረሰባዊ ማንነትን የቆየውን ታሪክና ማንነት በመሰረዝ እንደገና በአዲስ ታሪክና ማንነት የመተካትና ከኢትዮጵያ የማራራቅን አቅጣጫ፣ በሌላ በኩል ደግሞ ኢኮኖሚና ሃብት ግንባታ በተመለከተ የኤርትራ ተጠቃሚነት በሚያረጋግጥ መልኩ ከኢትዮጵያ ጋር የነበረውን ያልተመጣጠነ ግንኙነት ለማስቀጠል የሚያልም ሁለት ተቃራኒ አቅጣጫዎች (በአንድ በኩል የመራቅ በሌላ በኩል የመቅረብ) ግን ደግሞ ሁለቱ ተደምረው ኤርትራን ብቻ እንዲጠቅሙ የተቀመሩ ፖሊሲዎች ነበሩ። ወታደራዊ ዓቅሙ ለመገንባት ገና ከጥዋቱ ጀምሮ የተሰጠው ከፍተኛ ትኩረትም እነዛን ሁለት-አቅጣጭዮሽ ፖሊሲዎች ለማስፈጸም ታስቦ እንደሆነ ግልጽ ነው። ይህን ለመገንዘብ ኤርትራ ብርን ትታ ናቅፋ የተሰኘ የራሷን ገንዘብ አትማ ለመጠቀም የወሰነችበትን ሁኔታ እንይ። ኤርትራ ቀድሞውንም የብርን ምንዛሬ ከህግ ውጭ በመተመን በራሷ የዋጋ ተመን ስትመነዝር እንደነበር ይታወቃል። ይህ ሲሆን የኢትዮጵያ መንግስት ተቃውሞ አላሰማም። ኤርትራ ከኢትዮጵያ የገዛቻቸው ምርቶች መልሳ ወደ ውጭ እንድትልክ ያስቻላት መንገድ የተፈጠረውም በዚሁ እሷ ራሷ በተመነችው ዝቅ ያለ የብር-ዶላር የልውውጥ ዋጋ ነው። ይህ ብቻ ሳይሆን ማናቸውም በሬሚታንስና በኅብኘዎች በኩል የሚገባው ዶላር በኤርትራ በኩል ወደ ብር ተመንዝሮ ነበር የሚመጣው። ከዚህ በኋላ በርካሽ ዋጋ የተሰበሰበው ብር ኢትዮጵያ ውስጥ ወዳሉት ባንኮችና ገበያዎች በአካል ተቀላቅሎ እንደገና ሌላ ከፍ ያለ ዋጋ ይላበሳል። ኤርትራ ይህንን በብዙ መንገድ ተጠቃሚ የሚያደርጋትን የገንዘብ ስርዓት ለመቀየር ትፈልግ ነበር ብሎ ማሰብ ፈጽሞ ምክንያታዊ አይሆንም። ይሁንና የኤርትራ መንግስት የነበረው የጥቅም ብልጫ ሳይነካ በአንድ በኩል አዲስ አገራዊ ማንነት ለመገንባት የናቅፋ ካሬንሲ የሚኖረው ፖለቲካዊ የማንነት መገለጫ፣ በሌላ በኩል ደግሞ በነበረው የምንዛሪና የንግድ ጥቅሞች ላይ የራስን ገንዘብ በፈለጉት መጠን የማተምና የማሰራጨት ስልጣን ለመቀዳጀትና ጥቅሞችን በእጥፍ ድርብ ለማስፋት የተዘየደ ውሳኔ እንደነበር በቀላል ማሰብ ስሌት የሚገኝ እውነታ ነው። ኤርትራ የገነባችው ከፍተኛ ወታደራዊ ኃይል ኢትዮጵያ ይህንና መሰል ሁኔታዎችን ለመቃወም እንዳታስብ፣ ካሰበች ደግሞ እንዳትገፋበት፣ ከገፋችበት ደግሞ ለውጥ እንዳታመጣበት የመጨረሻው አማራጭ ተደርጎ ተወስዷል። ሁኔታዎች ወደዚህ ደረጃ እንዳመሩ የተከሰተው ግጭትና ጦርነት በዚህ መልኩ የመጣ ነው። የኃይል ማሳያው የመጀመሪያ ቦታ ባድመ ብትሆንም ባድመ ድንበር ላይ ስላለች ብቻ ጦርነቱ የድንበር ጉዳይ ነበር ማለት አይደለም። እርግጥ የኢትዮጵያ መንግስት ለራሱ ህዝብም ለዓለምም ይፋ ያደረገው ስሞታ "ግዛቴ ተወረረ፣ ሉዓላዊነቴ ተደፈረ" የሚል ነበር። የኢትዮጵያ መንግስት ምን እንደተከሰተ አቤቱታ ከመግለጽ ውጭ ችግሩ የተፈጠረበት ምክንያት መልስ መስጠት ያለበት ክስተቱን የፈጠረው አካል ነው ከሚል እሳቤ ሊሆን ይችላል። ሆኖም የኤርትራ መንግስት ከድንበሬ አልፌ አልወረርኩም በማለቱ ክርክሩና ማስረጃው የወረረው ለማወቅ ድንበሩ የት ነው ወደሚል አመራና ግጭቱ የድንበር ግጭት ጉዳይ ሆኖ ወጣ። ድርድሩም፣ ሽምግልናውም፣ ችሎቱም በአጠቃላይ ሁሉም የሰላምና የግልግል ጥረቶች የድንበር ይዞታ በመለየት እንደሚፈታ ችግርና ግጭት አድርገው ወሰዱት። ባድመ በግጭት መነሻነቷ፣ በይዞታዬ ናት ፕሮፖጋንዳ፣ በጦርነት ምክንያት ለተከፈለው

መስዋእትነት ሰበብነቷና ለውድመቱና መገዳደሉ በምታስከትለው ተጠያቂነት ምክንያቶችና በሌሎችም ተዛማጅ ሁኔታዎች የተጋነነ ፖሊቲካዊ ስብእና እንድትላበስ ሆነ። የኮሚሽኑ ውሳኔ የጦርነቱ መነሻ የሆነችውንና እስከ ኤርትራ ወታደራዊ ወረራ ድረስ የኢትዮጵያ ይዞታ የነበረችውን፣ ወረራውን ለመቅለበስና በኃይል የተያዘውን መሬት ለማስለቀቅ በተካሄደው ጦርነት የኢትዮጵያ መንግስት በከፍተኛ መስዋእትነት ያስመለሳት ባድመ ግን በድንበር ኮሚሽኑ ውሳኔ ወደ ኤርትራ በመካለሏ ምክንያት ግጭቱ ብቻ ሳይሆን ግልግሉም ተወሳሰበ። ከወጡ ሳይሆን ከጉልቻው ባለ **5** ነጥቡ የሰላምና የድርድር ጥሪ የቀረበው እንግዲህ ይህ ሳይቋጭና ወደ ሰላማዊ ጉርብትና ሳይመለሰን ተንጠልጥሎ የቀረውን ጉዳይ ከእውነተኛ የግጭቱ መንስኤዎች ጋር በማያያዝ የተሟላና መልክ ያለው ዘላቂ መፍትሄ ለማበጀት ታስቦ የቀረበ ጥሪ ነበር። ባድመን ለኤርትራ እንድትካለል ያደረገው የኮሚሽኑ ብይን ከቀረበለት የመከራከርያ ሙግትና ጭብጥ አንጻር **"**ርትዓዊ ውሳኔ ሰጥቷል፣ አልሰጠም**"** ብሎ መከራከር አሁን ምንም ትርጉም አይኖረውም። ውሳኔው ግን ለኤርትራ መንግስት ያልታሰበ የፖለቲካ ሲሳይ የመሆኑን ያህል ለኢትዮጵያ ደግሞ እጅግ የሚጎመዝዝ እንደነበር ጥርጥር የለውም። ከድንበር ኮሚሽኑ ውሳኔ የኤርትራ መንግስት ሁለት ወሳኝ ጥቅሞች ተጎናጽፏል። አንደኛ **"**ጦርነቱ እኔ የፈጠርኩት ሳይሆን በቦታየ እያለሁ የመጣብኝና እኔም የመከላከል ጦርነት ውስጥለመግባትተገደድኩ**"** በማለት የኤርትራ ህዝብ የተከፈለው መስዋዕትነት በኤርትራ ጠብ ጫሪነት ያልመጣ ፍትሃዊ ጦርነት ነበር ብሎ ለማጭበርበር አሳሳች የሞራል መሳርያ አገኘ። ሁለተኛ ደግሞ በማይጣጣሙ ፖሊሲዎች ግጭት ምክንያት፣ ከዚያም በወራሪነት ከሶ፣ የኢትዮጵያን ህዝብ ከዳር እስከዳር አነሳስቶ፣ በመጨረሻም በፍልሚያ አሸንፎ ስላሳፈረው አምርሮ የሚጠላውን የኢህአዴግን መንግስትን የሚበቀልበት የፖለቲካ መሳርያ እጁ ዉስጥ እንደገባ ተገነዘበ። ይህም ተወረርኩ በማለት ልጆቻችን አስጨርሶ ባድመን አስረከበ ብሎ የኢትዮጵያ ህዝብ ሰለሚቆጣ ግንባሩና ህዝቡ ሆድና ጀርባ ይሆናሉ ከሚል ስሌት ጮቤ እንደረገጠ ይገመታል። የኤርትራ መንግስት እነዚህ ከላይ የጠቀስናቸውን ሁለት ወሳኝ ጥቅሞች አስጠብቆ ለመሄድ ጊዜው አልፏል ብሎ ካላመነ በቀር ይህንን ከአሰርት ዓመታት በላይ የዘለቀውን አቋሙን ቀይሮ ባለ **5** ነጥቡን የሰላምና የድርድር ሃሳብ ይቀበላል ብሎ ለማመን ያዳግታል። አመራሩ ዘላቂ ፋይዳ የሌለውን ፖሊሲ ሞክሮ ወይም ገምግሞ በተሻለ ገንቢ ፖለሲ በመቀየር አቅጣጫን የማስተካከል ባህል የተላበሰ አይደለም። ይልቁንም ፖሊሲው ሳይቀየርና ሳያስተካከል ይልቁንም ያልተሳካው ሙከራ የሚሰራበትን ሌላ መንገድ ለመፈለግ ከግልጽ እስከ ህቡእ፣ ከህጋዊ እስከ ወንጀል ያሉትን ዘዴዎች በመጠቀም ያንን ፖሊሲ ለማስቀጠል የማይፈነቅለው ድንጋይ እንደሌለ ደጋግመን አይተናል። ለምሳሌ ኢትዮጵያ የነበረውን ኢፍትሃዊ የገንዘብና የንግድ ግንኙነት ለማስተካከል ስትነሳ፣ ሁኔታዎችን ገምግሞ ሁለተኛው የተሻለ አማራጭ ፖሊሲ ቀይሶ እንደመቀጠል፣ የነበረውን ለማስቀጠል ወታደራዊ ጉሸማ ያስፈልጋል ብሎ ሁለቱንም ህዝቦች ከመልካም ተስፋና ገንቢ ጉርብትና ወደ መዳማትና ምስቅልቅል ወዳለ ውል የለሽ ሁኔታ እንዲያመሩ ዋናውን አፍራሽ ሚና ተጫወተ። ከጦርነት ፍጥጫ በኋላም ሁኔታዎችን በሚገባ ገምግሞ ወደኃላ እንደመመለስ ወታደራዊ የበላይነት አለኝ በሚል ስሜት የህግደፍ ፖለቲካዊ ውሳኔ የተፈጥሮ ህግ ያህል የማይሻሩና የማይደፈሩ እንደሆኑ **"**ፀሃይ በምዕራብ እንደማትወጣ ሁሉ እኛም ባድመን ለቀን አንወጣም**"** ሲሉ ተናገሩ። በውግያ ተሸንፈው ከወጡ በኃላም ባድመን ለማስመለስና የፕረዚዳንት ኢስያስ ቃል ከሚሰበር የኤርትራ ወጣት ይሰበር**"** ዓይነት በብዙ ድግግሞሽ ከየካቲት እስከ ሰኔ ወር እጅግ ዘግናኝ ዕልቂቶች ያልተለያቸውና ያልተሳኩ ማጥቃቶች አካሂደው ነበር። የህግዴፍ መሪዎች በተለይም አቶ ኢሳያስ ጦርነቱ በአጠቃላይ የኃይል ሚዛኑን ለውጦ ኤርትራ ተሸናፊ ከሆነችና የአልጀርስ የሰላም ስምምነት ከተፈረመ በኋላም አንዴ በሶማሊያ ሌላ ጊዜ ከውስጥ እያለ ስልቶቹን የማቀያየር ጉዳይ ካልሆነ ከኢትዮጵያ ጋር ያለው የተበላሸ ግንኙነት አክሳሪና ለሁለቱ ወንድማዊ ህዝቦች የማይገባ ስለሆነ መቀየር ያለበት ነው ከሚል አርቆ ማሰብ ሁኔታዎች ገንቢ አቅጣጫ እንዲይዙ ለማድረግ አንዲት ስንዝር አይጓዙም። ሌላ አስረጅ ቢያስፈልግ፣ የኤርትራ መንግስት ለ **18** ወራት የሚቆይ ሲል በይፋ ያወጀው የግዳጅ አገራዊ አገልግሎት ፕሮግራም

እንዳለው ይታወቃል። ፕሮግራሙ የኤርትራ ወጣቶች በሙሉ ወደ ወታደራዊ ስልጠናና አገልግሎት እንዲሄዱ የሚያስገድድ ሲሆን እስከአሁን በአስሮች የሚቆጠሩ ዙሮች ገብተው ስልጥነው ወደየአገልግሎት ምድባቸው ይሰማራሉ። ይሁንና መግባት እንጂ መውጣት፣ መሰለፍ እንጂ መሰናበት የለም። ብዙዎቹ ኤርትራውያን ይህንን አስከፊ ስምሪት **"**ባርነት**"** በሚል ቃል ይገልጹታል። መግለጽ ብቻ አይደለም፣ በየወሩ በሺዎች ደረጃ አገራቸውን ጥለው እየሸሹ ይወጣሉ። ወጣቶቹ ገና ከኢርትራ ሳይወጡ ድንበሯን ሳያልፉዋት **"**የሚሸሹ ካያቹህ ተኩሳቹህ ግደሉ**"** የሚል ቀዋሚ መመርያ በተሰጣቸው የኤርትራ ወታደሮች የመገደል አደጋ እንዳለ ያውቃሉ። ገድ ገጥሟቸው በህይወት ወደ ሱዳን ወይም ወደ ኢትዮጵያ ቢሻገሩም የሚቆዩት ምቾት አልባ በሆኑት የስደተኞች መጠልያዎች እንደሆነም ይገነዘባሉ። የካምፕ ኑሮና የተሰፋ ጥበቃ ሲሰለቻቸውም ወደ አውሮፓ ወይም ወደ እስራኤል በህይወት የማይተርፉበት ሰፊ አደጋ እንደሚገጥማቸው እያወቁ ዕድላቸውን ይሞክራሉ። የኤርትራ መንግስት መሪዎች ይህ ሁሉ ቢሰሙም፣ ለብዙ የኤርትራ ወጣቶች ሽሽትና መቅዘፍት ምክንያት የሆነውን አገራዊ አገልግሎት ማቆም ወይም ማሳጠር በሚል አልቀየሩትም። ከዚሁ ጋር የሚደመር ሌላ ምሳሌም አለ። በቅርቡ አውሮጳ በስደተኞች ብዛት ተማርራ ከኤርትራ መሪዎች ጋር መግባባት ላይ ይደረሳል። የአውሮፓ ህብረት **200** ሚልዮን ዶላር ለኤርትራ በእርዳታ ሊሰጥ፣ ኤርትራ በበኩሏ ስደተኞች ከአገራቸው ሳይወጡ ተስፋና ስራ የሚያገኙበት፣ የአገራዊ አገልግሎት ዘመንም በህጉ መሰረት ወደ **18** ወር እንዲያጥር ነበር መግባባቱ። አውሮፓ በተባለው መሰረት ገንዘቡን ፈቀደች። ኤርትራ ግን አሁን ባለፈው ሳምንት ገደማ የአገራዊ አገልግሎት ዘመን ላልተወሰነ ጊዜ እንደነበረው ማለትም **"**ገብቶ ያለመውጣት**"** ሆኖ ይቀጥላል ስትል ዕቅጩን ተናገረች። እነዚህ የተጠቀሱት የኤርትራ መንግስት መጥፎ ፖሊሲዎችን ማስተካከልና መቀየር ፈጽሞ የሚታወቅበት ባህል እንዳይደለ ለማሳየት ነው። የኤርትራ መንግስት ከስጋት ወደ ማንሰራራት የኤርትራ መንግስት ፖሊሲውን የሚቀይር ቢሆን ያንን እንዲያደርግ በወሳኝ ምክንያቶች የሚገደድባቸው ወቅቶች ሁኔታዎች ነበሩ። ለምሳሌ በ **2000/1** ወይም በ **2005/6** ወይም በ **2008-10**። በ **2000/1** ኤርትራ የነበረውን ከኢትዮጵያ ስታገኘው የነበረውን ጥቅሟን ለማስቀጠልና ለማስፋት የኃይል ጫና ያስፈልጋል ብላ በማሰብ በተሳሳተ ስሌት ከኢትዮጵያ ጋር የገባችውን ጦርነትበሽንፈት ሲጠናቀቅ ቆም ብላ ራሷን ፖሊሲዋን መፈተሽ የነበረባት ወቅት ነበር። ወደዛ ዓይነት ጦርነት ያደረሰውን መንገድ የኤርትራ ተጋፊና ሚሊቴራይዝድ ቁመና አስተሳሰብ ነበር። ያ ደግሞ እንደታሰበው ወደ ውጤት ሳያደርስ ተንኮታኩቶ ሲከሽፍ ኤርትራ አቋሟንና መንገዷን እንድትቀይር የሚገፋፋ ትክክለኛ ወቅት ነበር። በ **2005/6** ኤርትራ የድንበር ኮሚሽኑ ውሳኔ ያለ ንግግርና ያለኢትዮጵያ ይሁንታ እንደማይፈጸም በማወቅ አንሚን ካባረረች በኋላ፣ የድንበር ኮሚሽኑም ከተበተነ በኋላ፣ በሶማልያ የተከፈተው የውክልና ግንባር ከከሸፈ በኋላ ኤርትራ አቋሟንና መንገዷን ማስተካከል ነበረባት። በ **2008-10** ከተለመደው አሰራር ማፈንገጥ በመገለልና ማዕቀብ እንደሚያስቀጣ በተግባር ያየችበት ጊዜ ነበር። ከሁሉም በላይ ደግሞ የኤርትራ ኢኮኖሚ ክፉኛ አሽቆልቁሎ እንደአገር በገንዘብ በተለይም በምንዛሪ እጥረት የተሽመደመደችበት ወቅት ስለነበር ለነዳጅና ደመወዝ መክፈል የተቸገረችበት ወቅት ነበር። በነዚያ ወቅቶች የኤርትራ ኤክስፖርት ከ **14** ሚልዮን ዶላር አይበልጥም ነበር። ከሊቢያ ሲገኝ የነበረውንም ድርጎ ያቆመበት ጊዜ ነበር። አሁን ኤርትራ በተለየ ሁኔታ ውስጥ ነው ያለችው። ከማዕድን ምርት ብቻ እምታገኘው ገቢ እስከ **450** ሚልዮን ዶላር ይደርሳል። ሌሎች ሶስት የማዕድን ማምረቻ መስኮችም እየተከፈቱ ስለሆነ ይህ ገቢ እያደገ የሚሄድ ነው። በስዊዝ ባንክ **(HSBC SWISS BANK)** ውስጥ አስመራ በሚገኙ ሁለት ግለሰቦች ስም **700** ሚልዮን ዶላር መቀመጡን አንበናል። አስመራ ውስጥ ያን ያህል ሃብት የገነባ ሰው ስለሌለ የመሪዎቹ አለያም የግንባሩ እንደሆነ መገመት ስህተት አይሆንም።የኤርትራ መንግስት ብዙ ሌሎች የጨለማ ስራ ገቢዎችም አሉት። ለብዙ መንግስታት በውክልና የሚሰራቸው የማቀባበል አገልግሎት እየሰጠ ኪራይ ይቀበላል። የግብጽ መንግስት በፖለቲካው አፓራተስ የሰላምና የድርድር አቅጣጫ የተከተለ ቢመስልም ይህ አንድ ውጤት ወይም ለውጥ ላይ እስኪደርስ ድረስ የጸጥታና የደህንነት መዋቅሩ አሰራርና

ስምሪት የሚንቀሳቀሰው "ኢትዮጵያን ማስቸገር" በሚለው ሲወርድ ሲዋረድ በመጣው ቅኝት ነው። ከዚህ አንጻር ቁጥር አንድ ኪራይ ተቀባይ የኤርትራ መንግስት ሲሆን በዚህ ደረጃ የጥቅም ተካፋይ ለሚሆኑ የኢትዮጵያ ጽንፈኛ ተቃዋሚዎቹም ከሚያገኘው እያቀናነሰ ያስተላልፋል። የመን አካባቢ የነደደው እሳት ለኤርትራ መንግስት መልካም ሆነለት። ኳታር፣ ሳውዲንና ኤሜሬትስ ለመሳሰሉ ክንፋቸውን በመዘርጋት ላሉት ሃብታም አገሮች በየመን ብቻ ሳይሆን በአፍሪካ ላሉዋቸው ኢ-ጨዋ ለሆኑ ስራዎች በአስፈጻሚነት ይሰራል። ቀይባህር አረባይዝድ እየሆነ ነው። የአሰብ ወደብ የግመል መጠጫ ይሆናል የተባለውም ትክክል የሚሆነው የሳውዲና የኤሜሬትስ ግመሎች ለማለት ከሆነ ነው። ለዚህም አንድ ታዛቢ እንዳሉት ጥሩ "የሰይጣን እጅ ኪራይ" ይቀበላል። የታወቁ የፖለቲካ ተንታኝ አሌክስ ዴ ዋል እንዳሉት የኤርትራ መንግስት ዋና ስራውና ተልእኮው መገለጫ ሞዴል እንደማንኛውም መደበኛ መንግስት የፖሊቲካ አመራርና አስተዳደር ሳይሆን የተወሳሰበ "መንግስታዊ ፖለቲካዊ ቢዝነስ ማስፋፋትና ጂኦፖለቲካዊ ኪራይ መሰብሰብ" ሆኗል። የፖላቲካ ኪራይ ስብሰባውም አገር ውስጥ ካሉት የሰውና የዕቃ ዝውውር ኮንትሮባንድ በኪራይ ዋጋ ከማስፈጸም ጀምሮ ለተለያዩ አህጉራዊ ኃይሎች (አሸባሪዎችንም ይጨምራል) ገንዘብና መሳርያ እስከማቀባበል፣ መሬትና ወታደራዊ አገልግሎትን እሰከማከራየት የሚደርስ የደራ "አዋጭ" ቢዝነስ ነው። እነዚህ ሁኔታዎች እስካሉ ድረስ የኤርትራ መንግስት ሚና ከዚህ የተለየ አይሆንም። እነዚህ ሁኔታዎች ደግሞ መልካቸው ቢቀይሩ እንጂ በዛላቂው ከአካባቢያችን ይወገዳሉ ማለት ከየዋህነት የሚቆጠር ይሆናል። ይህን ሁሉ መጥቀስ ያስፈለገው፣ የኤርትራ መንግስት ምን ያህል "የተደላደለ ሁኔታ" ውስጥ እንዳለና ይህንን አቋሙን ለመቀየር የሚያተጋው ምንም ዓይነት ምክንያት እንደማይታይ ለማብራራት ያህል ነው፡፡ ተጨባጭ እውነታው ይህ ከሆነ የኢትዮጵያ መንግስት አንድ ለአስር ዓመታት ያህል የቆየና የኢትዮጵያና የኤርትራ ግንኙነት በማሻሻል ረገድ ውጤት ያላመጣን ፖሊሲ እንዳለ ይዞ መቀጠሉና በምትኩ በሌላ አዲስ ፖሊሲ ለመቀየር ያልሞከረበት ምክንያት ምንድነው? የመደጋገፍ እርግማን ትሥሥር ኤርትራ ኢትዮጵያን የመጥቀምም የመጉዳትም ተጨባጭ አቅም አላት። የኢትዮጵያ መንግስት ዋና የስራ ኃላፊነት የኤርትራን ፖለቲካዊ ህልውናና ቁመና ከአሉታ ወደ ገንቢ፣ ከጎጂ ወደ ጠቃሚ ሁኔታ ማሻገር ነው። ይህን እውነታ ተቀብሎ አስፈላጊ ሃብትና እውቀት በማሰማራት ያንን ሽግግር እንዲፈጸም ማድረግ የኢትዮጵያን ህዳሴ ማፋጠን፣ የኢትዮጵያን ጥንካሬ ማረጋገጥ፣ የኢትዮጵያን ተጋላጭነት መቀነስ ማለት ነው። የኢትዮጵያና የኤርትራ የዝምድና ትብብር ባህርይ ሊሆን ይገባው ከነበር አንጻር ሲታይ አሁን ያለው ሁኔታ ከዚያ ተቃራኒ ነው። በኤርትራ ጉዳይ ላይ ከኢትዮጵያ እኩል መጨነቅ ያለባት ሌላ አገር ልትኖር አትችልም። ኢትዮጵያና ኤርትራ በተፈጥሯዊና ህብረተሰባዊ ሁነታቸው ለመደጋገፍ እንጂ ለመወዳደር ወይም ለመቀናቀን የተቀረጹ አገሮች አይደሉም። ለዚህም ነው "በመደጋገፍ እርግማን የተቆራኙ ጎረቤቶች" የሚባሉት። አሁን ያለው የተቆራረጠና የጸብ ግንኙነት ከተፈጥሮአቸው ውጭ ነው። "ፖሊስያችን አልቀየርንም፣ አንቀይርም" ማለት የሚከተሉትን ስህተቶች እየፈጸምን ለመሆኑ ግልጽ መሆን አለበት። ላለፉት አሰርት ዓመታት እስከ አሁን ያልተለዩንን የኤርትራ መንግስትስን አዋኪና ተንኳሽ ተግባራት አላስቀረንም። ሁለቱ በደም ጭምር የሚዛመዱ ህዝቦች በመካከላቸው የመረብ ወንዝ ብቻ ሳይሆን የጠላትነት ወንዝ እንዲፈስ ዕድል እየሰጠን ነው። ቀጠናችን የአስተማማኝ ሰላምና ስምምነት በማድረግ የሁለቱንም ህዝቦች በኢንቨስትመንትና በቱሪዝም የሃብት ፍሰት በመሳብ እንዲሁም ከደህንነት አንጻር ሊኖራቸው ይችል የነበረውን ተስፋና ጥቅም ሲመክን እንደ አንገብጋቢ ኪሳራ አልቆጠርነውም። የኤርትራውያንን ፍልሰትና እንግልት እንዲሁም ኤርትራን ወደ ሙሉ ጣራ-የለሽ እስርቤተነት የቀየረን የኑሮ ሁኔታ ለመቀየር የሞራል ኃላፊነት ያለን ህዝብና አገር መሆናችን ዘንግተናል። ይህም በአንድ ጹሁፍ "ስንፈተ መንግስት" በሚል ለገለጽኩት ድክመት አንዱ ማሳያ ተደርጎ ሊታይ ይችላል። ዳውላና ዱላ ወደ መፍትሄው እንምጣ። መፍትሄዎች ሁሌም ያለውን ሁኔታ ከማስተካከል እስከ መተካት አማራጭነት የሚያዩ መሆን አለባቸው። ይህም ሲባል ፈረንጆች ዳውላና ዱላ **(carrot and stick)** የሚሉት ዓይነት ነው። ማስተካከል ከመተካት የቀለለና አነስ ያለ ዋጋ የሚጠይቅ ነው።

መጀምርያ አሁን ካለው የኤርትራ መንግስት ጋር ለማስተካከልና ለመግባባት የሚያስችሉ ሁኔታዎችና አማራጮች እንፈትሽ። የኤርትራ መንግስት ከልቡ አለያም ለፕሮፖጋንዳ ፍጆታ ብሎ የሚያቀርበው ቅድመ ሁኔታ የድንበርና የባድመ ጉዳይ ነው። እንደውም የድንበር ጉዳይ በሚል ያነሷል እንጂ የቅድመ ሁኔታው መነሻና መድረሻ “የባድመ ጉዳይ” ነው። ከዚህ አጀንዳ በስተጀርባ ያለውንም የፖለቲካ ትርፍ እሳቤ ምን እንደሚመስል ቀደም ብዬ ለማብራራት ሞክሪያለሁ። በትክክል ባድመ የግጭቱ ውጤት እንጂ መንስኤ አይደለችም። የኤርትራ መንግስት የድንበር ማካለሉ ተግባር በችካል ደረጃ ሳይለይ አንሚን በማባረሩ፣ ጊዚያዊ የጸጥታ ቀጠናውን በማፍረሱ፣ ጸብና ትንኮሳ ባለማቋረጡ የአልጀርሱ አጠቃላይ የሰላም ስምምነትና ውልም ፈርሷል ለማለት የሚያስችሉ ህጋዊ ሁኔታዎች አሉ። ያም ሆኖ ግን ለዘላቂ የህዝቦች ጥቅምና ህዝቦቹ ከሰላማዊና መደበኛ ጉርብትና የሚኖራቸውን የበለጠና ትልቁን ብሩህ ዕድል ለመክፈት ሲባል የድንበሩ መካለል በኮሚሽኑ ብይን መሰረት ይፈጸም እንኳ ቢባል የባድመን የፖለቲካ ጃኖ በማንሳት ብቻ ነው መጀመር ያለበት። ይህም የሚሆነው የኤርትራ መንግስት ያለምክንያትና በተሳሳተ ስሌት የወረራ ጦርነት ስለመክፈቱ ለሁለቱም ህዝቦች በይፋ ይቅርታ መጠየቅ አለበት። ይህ እንዲሆን የሚያስፈልግበት ምክንያት አንድም እውነት ስለሆነና በካሳ ግልግል ኮሚሽኑ በግልጽ የተመሰከረ በመሆኑ ሲሆን ዋናው ምክንያት ግን ብይኑን ከመተግበር ጋር ጦርነትን የከፈተው አካል ባድመን ከማግኘት ጋር የማይገባውን የፖለቲካና የፕሮፖጋንዳ ጥቅም እንዳይሸመትበት ለማድረግ ነው። የኢትዮጵያ መንግስት “ኤርትራ መውረሯን የጦርነቱ ጀማሪ መሆኗን አምና ይቅርታ ትጠይቅ” የሚል ለድንበሩ መካለልም ለሌሎች ገንቢ ግንኙነቶችም በር ከፋች ነው” የሚል አቋም ቢያራምድ ተገቢ ነው። አንድም የሞራል ሸክሙን ለሚገባው ባለቤት መስጠት ማለት ይሆናል። ያንን የመሰለ ምክንያት የለሽና **70** ሺ ሰዎች ያለቁበት የወንድማሞች መፋጀት ማንም አካል ኃላፊነት ሳይወስድበት መቅረት የለበትም። አዲስ የድንበር መካለል ድርድርና ግልግል ይጀመር ከማለት ምናልባት የድንበር ኮሚሽኑ በሰጠው ብይን ይካለል እንኳን ቢባል “ታዲያ ባድመን ለማስመለስ ለምን ሞትን” በማለት ሊኖር ስለሚችለው የህዝብ ቅሬታ ወረራን የመቀልበስና ሉአላዊነት የመከላከል መስዋዕትነት እንደነበር ያስረዳል። በዚህ ላይ ጦርነቱ የተከፈተው በኤርትራ መንግስት እንደነበር ራሱ የኤርትራ መንግስት ይቅርታ በመጠየቁ የሚገነዘብ የኤርትራ ህዝብ “አገርህን ከኢትዮጵያ ወረራ ተከላከል” በሚል ሲሰማው ለከረመው ማደንቆርያ ፕሮፖጋንዳ እንደማርከሻ ያገለግላል። የኤርትራ መንግስት ለጦርነቱ ኃላፊነት ወስዶ ይቅርታ ለመጠየቅ የሚስማማበት ሁኔታ አለ ወይ**?** የዚህ ጥያቄ መልስ የፈለገ ቢሆን ኢትዮጵያ የይቅርታ ቅድመ ሁኔታ ማቅረቧ የእውነት፣ የኃላፊነትና የሞራል ሸክም ሸክሙን ሊሸከም ወደሚገባው ኃይል መግፋቷ ተገቢ ነው። የሞራልና የተጠቂነት ስልጣንና የበላይነት ያስታጥቃታል። ጥያቄው በመነሳቱ ራሱ፣ በተጠያቂው አካል ተቀባይነት ቢያገኝም ባያገኝም ቀላል የማይባል የእውነትና የአጀንዳ ባለቤትነት ያቀዳጃል። የኤርትራንም መንግስት ከአቤቱታ አቅራቢነት ወደ ተከላካይነት አፈግፋጊነት ይገፋዋል። ዋናው ቁምነገር ግን ያን ያህል ህዝብ የሞተበትና ስንት ሃብትና ዕድል የባከነበት እኩይ ጦርነት እንደዘበት ተዳፍኖ ማን ለኮሰው የሚለው ጥያቄ መልስ እንኳን ባያገኝ ቢያንስ ጥያቄው ሳይሞት እየተነሳ መቀጠል አለበት። የጥያቄው ባለቤት ኢትዮጵያ የመልሱ ባለቤትም የኤርትራ መንግስት መሆን አለበት። ስለዚህ የኤርትራ መንግስት በፈቃድኝነት ይቅርታን የመጠየቅ ኃላፊነት “ይወስዳል፣ አይወስድም” የሚለው ሳይሆን ኢትዮጵያ ተገቢ ጥያቄ በተገቢው ቦታና ሰዓት ማንሳቷ ነው። ስታነሳም በሶስተኛ ታዛቢ ተቀባይነት ያለው በቂ ምክንያትና ማስረጃ ይዛ ከሆነ ፍትሃዊ ነው። የኤርትራ መንግስት ፍትሃዊ የሆኑ ጥያቄዎች ቀርቶ ፍትሃዊ ያልሆኑ ጥያቄዎችን ተገዶ ሲቀበል አስተውለናል። በሌላ መንገድ ደግሞ ምንም ፍትሃዊ ቢሆን፣ ምንም ከከፋ ጥፋት የሚያድን ቢሆን፣ ምንም ዓይነት ዋጋ የማያስከፍልም ጥያቄም ቢሆን “በመቃብሬ ላይ” ያለበትና ከዚያም አልፎ ጭራሽ በጠያቂው ላይ ተጨማሪ ቅጣት ለመስጠት የሚንደረደርበት ሁኔታ እንደነበረ ስንታዘብ ኖረናል። ለምሳሌ ወረራው እንደከፈተ “ከባድመና ከሽራሮ” ወጥቶ ወደ ነበረበት እንዲመለስ ነበር የኢትዮጵያ ፓርላማ የመጀምርያው ጥያቄ። የኤርትራ መንግስት ያንን ቢያደርግ

ያለምንም ኪሳራ አውዳሚውን ጦርነት ማስቀረት ይችል ነበር። የኤርትራ መሪዎች ግን ያችን ትንሽ ግን ፈዋሽ እርምጃ ለመውሰድ አልፈቀዱም። ሩዋንዳና አሜሪካም፣ የአፍሪካ አንድነት ድርጅት ሸምጋዮችም የኤርትራ መሪዎችን የትዕቢት ክብር ሳይነኩ በተለያዩ አገላለጾች አለባብሰው ያች አነስተኛ እርምጃ እንድትወሰድ ኤርትራን ደጋግመው አባበሉ። ከሁሉም በላይ የፕረዚዳንት ኢሳያስ ባህርይ ጉልህ ማሳያ የምትሆነው ግን ከራሳቸው ሚኒስትር ከአቶ ባራኺ ገብረስላሴ ለቀረበላቸው ሃሳብ የሰጡት ምላሽ ነው። አቶ ባራኺ ያኔ በወረቀት ጽፎ የላከላቸው ማስታወሻ "ወያኔን እስከ አሁን በተደረገው ጦርነት ጥሩ አድረገን ቀጥተነዋል። ልኩን አሳይተነዋል። ይሁንና በሰላሙና በዲፕሎማሲው ጠረጴዛም ቢሆን እንዲሁ በሽንፈት እንዲቀጣ ማድረግ እንችላለን። ስለዚህ ለምን የሩዋንዳና የአሜሪካ የሰላም ሃሳብ ተቀብለን ድሎቻችንን አናስጠብቅም" የሚል ይዘት የነበረው ሃሳብ ነበር። ፕሬዚዳንት ኢስያስ ለሚኒስትር ባራኺ ጥያቄ በአንድ መስመር ጽሁፍ ምላሽ ሲሰጡ "የሚያጣድፍና እጅ የሚያሰጥ ምንም ምክንያት የለንም" የሚል ነበር። በኋላ ግን ከባድመም፣ ከዛላንበሳም፣ ከባረንቱም፣ ከተሰነይም ወጡ። በውጊያው መጨረሻ አካባቢ ያወጡት መግለጫም "ኢትዮጵያ ውግያውን ለመቀጠል የሚስችሏትን ሰብቦች ሁሉ ለማሳጣት፣ ከሚታወቁት ከአካራካሪዎቹ ቦታዎች ብቻ ሳይሆን ከማያከራክረው ከዓዲምሩግና ባዳም ጭምር ለቀን ወጥተናል" የሚል ሆኖ ተደመጠ። ሰሞኑንም ከድንበር አካባቢ ሆን ብሎ አፍኖ የወሰዳቸውን ሰላማዊ ዜጎች በጥድፍያ የመለሰበት ሁኔታ ልብ ይሏል። እነዚህ አስረጅዎች የሚሰጡን ስዕል የኤርትራ መንግስት ጥያቄዎችን የሚያስተናግደው በጥያቄዎቹ አግባብነት ምዘና ልክ ሳይሆን ጥያቄዎቹ በሚቀርቡበት ወቅት የኤርትራ መንግስት በሚታየው አደጋ መጠን የሚወሰን መሆኑን ነው። ይህም ማለት ለዚህ ዓላማ የሚያገለግል በኤርትራ መንግስት ላይ ዳውላ (የጋራ ጥቅም) አልታይ ካለ ዱላውን (ስጋት) ከፍ አድርጎ ማሳየት፥ ማሳየት ብቻ ካልበቃም እስከመጠቀም ለመሄድ የሚያስችል ዕቅድ ያስፈልጋል። በተለይም የኤርትራ መንግስት አጥጋቢ ምላሽ የሚሰጠው የስጋት ሁኔታው ከመሪዎቹ ፖለቲካዊ ህልውናው ጋር የሚያያዝ ሲሆን ነው። ዋናው ነጥብ፣ ሁለቱ አገሮች ወደ ሙሉ ሰላምና ሙሉ ጉርብትና እስኪመጡ ድረስ መፈንቀል ያለበት ድንጋይ ሁሉ መፈንቀል አለበት። ክቡር ጠ/ሚ/ር ኃይለማርያም ክቡር ጠ/ሚ/ር፣ ዞሮ ዞሮ አሁን ያለው የኤርትራ መንግስት ሁኔታዎቹን ወደ ተሻለና ገንቢ ሁኔታ የበኩሉን ለማድረግ ተባባሪ ሆኖ ካልተገኘ የህዝቦችና የአገሮችን መልካም ዕድል ላይ ቁማር እየተጫወተ፣ የህውከት ኪራይ እየሰበሰበ የሚቀጥልበት ዘመን እንዴት ማብቃት እንዳለበት መንግስትዎ ማሰብ፣ ማቀድና ለውጤት መስራት አለበት። ይህ ለማድረግ ጦርነት ማወጅ አያስፈልግዎትም። የኤርትራ መሪዎች በዓለም ማህበረሰብ ብቻ ሳይሆን በራሳቸውም ህዝብ የተጠሉ ናቸው። ለዚህ አባባል ጭብጥ ቢያስፈልግ በየቀኑ በአስመራ አውሮፕላን ማረፍያ ቤተሰቡ አበባ ይዞ የእንኳን ደህና መጣህ አቀባበል ከሚደረግለት ተመላሽ ይልቅ ጥይት እየተተኮሰበት በእግሬ አውጪኝ ወደ ስደት የሚወጣው ሰው በብዙ ዕጥፍ ቁጥር መብለጡ የሚያረጋግጠው ኀምዛዛ እውነት ነው። ይህ የሚሰደደው ህዝብ ለፍልሰት ከሚዳርገው ስርዓት መገላገል የሚፈልግ የለውጥ ፈላጊው ኃይል አካል ነው። የፕረዚዳንት ኢሳያስ ድርጅትና መንግስት ስልጣን ከያዘ ብቻ ሳይሆን በረሃ ከነበሩበት ጊዜ ጀምሮ ተቃዋሚ ፖለቲከኞችን ለአንድ ቀን እንኳ የአገራቸውን መሬት እንዲረግጡና ህዝባቸውን ቤተሰባቸውን እንዲጎበኙ ዕድል ያልሰጠ ድርጅትም፣ መንግስትም ነው። እነዚህ ሙሉ እገዛና ዕድሉ ቢያገኙ አገራቸንም ህዝባቸውንም ለመታደግ ማንኛውንም መስዋዕትነት ዋጋ ለመክፈል ፖለቲካዊ ሁኔታዎች እስኪፈቅዱላቸው ለረዥም ጊዜ ሲጠብቁና ሲዘጋጁ የቆዩ ናቸው። በውትድርናና ነጻ አገልግሎት ባርነት እየተሰቃየ አፍላ ዕድሜውን የተነጠቀው የኤርትራ ወጣትም ለውጥ አለዛም ራሱን ለማትረፍ መውጪያ ቀዳዳ የሚፈልግ ነው። ክቡር ጠ/ሚ/ር የኤርትራን ሁኔታ ለመቀየር አመቺ ሁኔታዎች አሉ። ከኤርትራ የመጡትን ወጣቶች በየስደት ካምፑ ለረዥም ጊዜ እንዲቆዩና እንዲደነዝዙ ከማድረግ አገራቸውን በትግል የሚረከቡበት ሁኔታ ለመፍጠር የሚስችላቸውን ሁለንተናዊ ድጋፍ መስጠት አንዱ መንገድ ነው። ሁለተኛው ተቃዋሚዎችን በኢንተሊጀንስ፣ በፕሮፖጋንዳና በሎጂስትስክስ፣ በአደረጃጀትና በስልጠና እንዲሁም በዲፕሎማሲ ሙሉ ድጋፍ በመስጠት የኤርትራን መንግስት በእኩል ወይም

በተቀራራቢ ዓቅም የሚታገሉበት ሁኔታ እንዲደርሱ ማስቻል ይገባል። የኤርትራ መንግስት በውጭ ያሉትን የራሱ ደጋፊዎች በተለይም የህዛባዊ ግንባር ለፍትህና ዲሞክራሲ ወጣት አባላት **(YPFDJ)** በሚል አቶ የማነ ገብረአብ በአምሳሉ የቀረጻቸው ጋሻ ጃግሬዎችንና በኮሚኒዩቲ መልክ ያደራጃቸው ደጋፊ ማህበረኮሞቹን በውጭ አገር የሚያደርጓቸውን የተለያዩ ህገወጥ ተግባራት እንዲጋለጡ በፍትህ ፈለጊ ተቃዋሚ አባላት የሚደረጉ ጥረቶችን መደገፍ ያስፈልጋል። የኤርትራ መንግስት እንደትልቅ የፕሮፖጋንዳ አቅም የሚጠቀምባቸው በውጭ ያሉ አክራሪና ጥገኛ ኢትዮጵያውያን ተቃዋሚዎችና ይህንን ሚና ለመጫወት በብዙ ባጀት የተዋቀሩ ሚድያዎች የሚነዙዋቸው አሉባልታዎችና የውሸት ማደናገርያዎች ለማምከን የሚያስችሉ መዋቅሮችንና አሰራሮችን መዘርጋትም ይገባል። የኤርትራን የፖለቲካ ሁኔታ በራሱ በኤርትራ ህዝብ ለመልካም እንዲለወጥ የኢትዮጵያ መንግስት ሙሉ ድጋፍና ቁርጠኝነት፣ እንዲሁም የተወሰኑ ተስፋ ሰጪ ለውጦች ከታዩ፣ ኤርትራውያን በአጣቃላይ፣ በተለይም ወጣቱ፣ አለፍም ሲል በታችኛው የመንግስት መዋቅር ውስጥ ያሉ ሞያተኞችና ዜጎች በሙሉ የለውጡን ትግል ይቀላቀላሉ። እርስዎና መንግስትዎም አሁን ያለው የኤርትራ መንግስት የፖለቲካና የሰይጣን እጅ ኪራይ ለመሰብሰብ እንዲመቸው በሁለቱ ህዝቦች የመተጋገዝና በሰላም አብሮ የማደግ ዕድል ላይ የፈጠረውን ጋሬጣ ላንዴና ለመጨረሻ በማስወገድ ታሪክ በመልካም ለውጥ ፈጣሪነትዎ ያስታውስዎታል። ዓለምም ይህንን በበጎ ማየት አይሳናትም። ክቡር ጠ/ሚ/ር፤ እንደ ኢትዮጵያና ኤርትራ ባሉ በጣም ቅርብና ወገን ህዝቦች ይቅርና ከሁሉም የኢትዮጵያ ጎርቤት አገር ህዝቦች ጋር ያለን ግንኙነት ዕጣ ፈንታ መወሰን ያለበት በብዙ ጥናቶችና የአማራጭ ሃሳቦች ፍተሻና ምዘና እንጂ፣ በጥቂት ፖለቲከኞች፣ ወይም ሹመኞች ዕይታና ይሁንታ መሆን የለበትም። በአጠቃላይም ያልተፈለገና አፍራሽ ግንኙነት ባጋጠመ ጊዜ ሁኔታዎችን ለመቀየር የሚያስችሉ በየዕለቱ አዳዲስ አማራጭ ሃሳቦች እየመነጩ፣ እየተጠኑና እየተተነተኑ ሊቀርቡ ሲገባ አንድ ሃሳብ ወይም ፖሊሲ (ያውም ግልጽ ውጤት ሳይኖረው) ሳይተካ ገዢ አቋም ለዓመታት እንዲንሳፈፍ ማድረግ የፖሊሲ ግብአቶች ድርቀት ያመለክታል። ሁኔታው አሁን ባለው አወቃቀር ያሉት የመንግስት ተቋማትም የየወቅቱና ዕለቱ የመንግስት አስተዳደራዊ ስራዎችና ፖሊሲዎች ለማስፈጸም ደፋ ቀና ከማለት አልፈው ስትራተጂክ ጉዳዮች ላይ ሃሳብ ለማፍለቅ እንዳልቻሉ ወይም እንደማይችሉ ያሳያል። ለዚህም ሲባል የጎረቤት አገሮችን መልካም ትሥሥር ስለመፍጠርና ከዚህ አንጻር ስለሚታዩ እንቅፋቶች እያጠና ለዘለቄታው ጠቃሚ ዕውቀትና መረጃ የሚያደራጅ፣ ለመንግስት እንደየወቅቱ፣ እንደየሁኔታውና እንደየጉርብትናው እየተነተነ ስለቅርብ ጎረቤቶቻችን ገንቢ የፖሊሲ ግብአት የሚያቀርብ ለምሳሌ የጎረቤት ህዝቦች የጋራ ብልጽግና ኮሚሽን ወይም **Neighborhood Revitalization Commission** የተሰኘ አንድ የጂኦፖለቲካዊ ጉዳዮች የሙያተኞች ስብስብ የማደራጀት ሃሳብ እንዲያጤኑት ሃሳብ በማቅረብ አጠቃልላለሁ።

ዳደ ደስታ-
ከኤርማይን ሚድያ

**dadeyom@gmail.com**